# ኅብረትን በተመለከተ ጥቂት ነጥቦች: ማስታወሻ ለልጅ ተክሌ

ታደሰ ብሩ

### *መንደርደሪያ*

ልጅ ተክሌ "ያጣነው ጥምረት አይደለም፤ ድፍረት ነው" በሚል ርዕስ በፃፈው ተገርሜም፤ አዝኜም አልወጣ ስላለኝ ጥቂት ማለት ፈለግሁ።

ተደጋጋሚ ሙከራዎች ስላልተሳኩ "ትብብር፣ ኅብረት፣ ግንባር፣ ቅንጅት፣ጥምረት" እና መሰል ቃላት ሁሉ የቫንኮቨሩን ልጅ ያንገሸገሹት ይመስላል።

እኔ ለልጅ ተክሌ የማቀርበው አቢይ ጥያቄ አለኝ - **ምግብ ቢያስጠላህ ምን ታደርጋለህ? —** የሚል። ከበሽታ እስከ ቁንጣን በተለያዩ ምክንያቶች ምግብ አስጠልቶን እናውቃለን ብዬ አምናለሁ። የምግብ ሽታ ራሱ ያስጠላን ጊዜም አይጠፋም። ግን እንዳስጠላን ቀረ? ምግብ አስጠልቶህ ወደ ምግብ የተመለስክበትን ሂደት አስታውስና በተመሳሳይ መንገድ ትብብርን ወደ መውደድ መመለስ ካልቻልክ - ልጅ ተክሌ - ችግር ላይ ነህ።

### ጥቂት ነጥቦች ስለ ኅብረት

እውነትህን ነው፣ ኅብረት ሁልጊዜ አስፈላጊ አይደለም። ማይክሮሶፍት ኦፊስ የሚያደለንን "ፍሪ ሴል" የሚባለውን የካርታ ጨዋታ ለመጫወት መተባበር አያስፈልግም። ይህ ጨዋታ የአንድ ሰው ጨዋታ ነው - ይበልጥ ትክክል ለመሆን ከተፈጥሮ ጋር የሚደረግ ጨዋታ ነው። ይህን ጨዋታ ለማሸነፍ የሚያስፈልግህ የራስህ ጭንቅላት ብቻ ነው። ጭንቅላት ያለው ባላንጣ የለብህም። ቴኒስ ስትጫወት ግን ሁኔታው ይለያል። ተፋላሚህ ጭንቅላት አለው፤ ልታደርግ ያሰብከውን ሊገምት ይችላል። እግር ኳስ ሲሆን ደግሞ የባሰ ውብስብ ነው። አንተም ወገን ጭንቅላቶች አሉ እዚያም ወገን ጭንቅላቶች አሉ።

ልጅ ተክሌ፣ የትብብርን አስፈላጊነትና አላስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን የትብብሩንም መጠን የሚወስነው የጨዋታው ዓይነት ነው። ስለትብብር ከመፃፍህ በፊት "እየተጫወትነው ያለው ጫወታ ምንድነው?" ብለህ መጠየቅ የነበረብህ ይመስለኛል።

በእኔ እምነት ወያኔ በ70ዎቹና በ80ዎቹ ያደረገው ትግል እና እኛ ዛሬ የገባንበት ትግል አንድ አይነት "ጫወታዎች" አይደሉም። ሌላው ቀርቶ በ97 በቅንጅት ወቅት የነበረው "ጨዋታ" እና የአሁኑ "ጨዋታ" ለየቅል ናቸው። እናም የሚፈልጉት የትብብር ዓይነትና ደረጃ ይለያያል።

### ስለ ኅብረት ጠቀሜታ

ትብብሮች ሊያመጡት ስለሚችሉ ጉዳቶች ነግረኸናል፤ ልዩነቶች ቢኖሩኝም በአብዛኛው ስለምስማማ አልፈዋለሁ። ስለ ትብብሮች ጠቀሜታ መናገር የኔ ድርሻ ይሁንና ሶስት ነገሮችን ብቻ ላንሳ።

1. **የግብህ ከባድነት።** ይህ በጣም ግልጽ ይመስለኛል። ብቻህን የማታሳካውን ግብ ከሌሎች ጋር ሁነህ አሳካ። (አንተ ግንቦት 7ን በሚመለከት ያየኸው ይኸንን ነጥብ ብቻ ነው። እናም ግንቦት 7 ሌሎችን ለትብብር መጋበዙ የራሱ ደካማነት ስለታየው ነው ብለሃል። ተሳስተሃል፤ የሚቀጥሉትን ነጥቦች ለማንበብ ትዕግሥት ይኑርህ።)

2. **የግብህ ትልቅነት።** አንዳንድ ውጤቶች ስንጋራቸው ዋጋቸው ይጨምራል። እስቲ አስበው!!! ግንቦት 7 ብቻውን ወያኔን ቢያሸንፍ "ድል" ይባላል? ግንቦት 7 "ወያኔ ቁጥር 2" እንደማይሆን ማረጋገጫችን ምንድነው? ለሰላማዊና ህጋዊ ትግል ከሚቀርቡ ክርክሮች አንዱ "በጉልበት የመጣ ራሱ ጉልበተኛ ይሆናል" የሚል እንደሆነ ታውቃለህ። ይህ ክርክር ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እውነት አለበት። እዚህ አዙሪት ውስጥ እንዳንገባ መከላከያችን ድልን

*መጋራት ነው። ለግብህ ከልብህ ዋጋ ስትሰጥ ድልህን ትጋራለህ። ድልን መጋራትህ በራስህም በሌሎችም ተባባሪዎችህ ላይ የምታጠልቀው መጠባበቂያ ነው።*

3. ***ሲነርጂ*** *(የአማርኛ ቃሉ ስለጠፋኝ ይቅርታ) ሰዎች ወይም ቡድኖች ተባብረው ሲሰሩ የሚያመጡት ውጤት በየግላቸው ተሯሩጠው ከሚያመጡት ውጤት ድምር በላይ ሲሆን “ሲነርጂ” ተፈጠረ እንላለን። ይህ ትርጓሜ ተቀባይነት ቢኖረውም በቂ ግን አይደለም።*

   *እኔ የምወደውን ትርጓሜ በምሳሌ ላስረዳ። አንተ “ከሁሉ የተሻለ ነው” የምትለው መንገድ አለ። እኔ ደግሞ “ከሁሉ የተሻለ ነው” የምለው ሌላ መንገድ አለ። እኔና አንተ ተገናኝተን ስንነጋገርና ስንከራከር ከኔም ካንተም የተሻለ ሌላ መንገድ አገኘን እንበል። አዲሱ መንገድ ለኔም ላንተም አዲስ፣ ለኔም ላንተም የተሻለ መንገድ ሆኖ አገኘው። ይህ ነው እኔ የሲኔርጂ ውጤት የምለው። እንዲህ ዓይነት ውጤት ትብብና ፉክክር (አስተውል ትብብርም ፉክክርም አብረው ባሉበት) ሁኔታ ብቻ ነው የሚገኘው። ሲነርጂ ሁሌ የሚገኝ ነገር አይደለም። ሲነርጂ እንዲፈጠር ግን የትብብርና ፉክክር መኖር ግድ ነው።*

   *ስለኅብረብሄራዊና የብሄር ድርጅቶች ዘይትና ውሃነት ከሌሎች ስሰማው የቆየሁ ቢሆንም እንኳን ካንተ ስሰማው አስደንግጦኛል። እንዳንተ “ምን አለ ትሉኛላችሁ” ማለትም አልፈቅድም። ሆኖም ግን ለሁለቱም የሚመች ጎዳና ካልተገኘ የኢትዮጵያችን ችግር መፍትሄ ያገኛል ብዬ አላምንም። ለሁለቱ የሚመች ጓዳና ማግኘት የእኔም ያንተም የጋራ ኃላፊነት ነው።*

### የአስተባባሪ ሚና

*ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች መዋሃድ እንደሚኖርባቸው ወትውተሃል። ወንድሜ መዋሃድን ተወውና ቀላል የሆነው መተባበርንም ስለተፈለገ ብቻ አይመጣም።*

*አሁን ማስታወስ አቃተኝ እንጂ በኬሚስትሪ ብዙ ምሳሌዎች ነበሩ። “ቅመሞችን” አመጣጥነህ በጠርሙስ በመክተት “በራሳቸው ተነሳሽነት” ተዋህደው አዲስ ነገር እንዲፈጥሩ አንድ ሺህ ዓመት መጠበቅ የሚኖርብህ እጅግ ዘገምተኛ ሪአክሽን። ለአንዳንዱ ታድያ ዘዴ አለው፣ ካታሊስት ትጨምርበታለህ። ሺህ ዓመት ይፈጅ የነበረው ሂደት በአምስት ደቂቃ ተጠናቆ ቁጭ ይልልሃል። ካታሊስትህንም ሳይቀንስ ሳይጨምር ታገኘዋለህ[1]።*

*ማኅበረሰብ ውስጥም እንደዚህ ነው። ድርጅቶች መተባበር ሲኖርባቸው ባለመተባበራቸው የድርጅቶቹን መሪዎች መውቀስ የተለመደ የሰነፍ ሥራ ነው። ማነው የማገናኘትና የማቀራረብ፣ ሰነዶችን የማዘጋጀት ሥራ መሥራት የነበረት? ማነው ቦታ አዘጋጅቶ፣ አጀንዳ ቀርጾ ማወያየት የነበረበት?*

### ማሳረጊያ

*የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ “ከኔጋቲቭ አስር እና ከፖዘቲቭ አስር የትኛው ይሻላል?” ብዬ ስጠይቅ የክፍላችን ተማሪዎች በሞኝነቴ እየሳቁ “ፖዘቲቭ አስር ነዋ!” ሲሉ ጮኹ። መምህራችን ግን በጥያቄዬ ተደምመው ብዙ ከቆዩ በኋላ ሲስቁ የነበሩትን ሁሉ ግራ ያጋባ ምላሽ ሰጡ። “ከኔጋቲቭ አስርና ከፖዘቲቭ አስር የቱ እንደሚሻል እንዲሁ መናገር አይቻልም። ለምሳሌ ጽድቅ ሥራ ከሆነ ፖዘቲቭ አስር ይሻላል። ኃጥያት ከሆነ ደግሞ ኔጋቲቩ ይሻላል። ኔጋቲቭ አስር እዳ እና ፖዘቲቭ አስር ሃብት እኩል ናቸው። ልጆች ሁሉም ነገር እንዲህ ነው። ጥሩ ወይም መጥፎ ለማለት አትቸኩሉ፣ በመጀመሪያ ምንድነው ብላችሁ ጠይቁ።”*

---

[1] . ቃሉን ስላልወደድኩት አልተጠቀምኩበትም እንጂ የ9ኛ ክፍል የኬሚስትሪ አስተማሪያችን Catalist “አጫፋሪ” ብለው ተርጉመውልን ነበር። በነገራችን ላይ በአፃራዊ መልኩ የ97ቱ ቅንጅት ውጤታማ የሆነው ካታሊስት ስለነበር ነው። ያ ባይሆን ኖሮ ፕሮግራማቸው አንድ ዓይነት ቢሆንም እንኳን መኢአድና ኢዴፓ አብሮ ለመሥራት መቶ ዓመት ይፈጅባቸው ነበር ይሆናል።

መምህሬን እድሜዓቸውን ያርዝምልኝ። ይህንን ማለታቸውን አያስታውሱት ይሆናል። እኔ ግን ዛሬ መልዕክታቸውን ለልጅ ተክሌ አስተላልፌዓለሁ። "ጥምረት አይረባም" ብሎ እርግጠኛ ሆኖ ከመናገር ይሰውረን። "ለመሆኑ ጥምረት ማለት ምን ማለት ነው?" ብሎ የመጠየቅ ብልህነትም ይስጠን።

አሜን።

ሴፕተምበር 9፣2010